# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ማኅበር ምሥረታ አስፈላጊነት

ከብርሃን ጌትነት አየለ

የማይለመድ ነገር የለም ቀስ በቀስ ሁሉንም ተላመድነው ። ሲያንገላቱን ዝም ፣ ሲያፈናቅሉን ዝም ፣ ሲገሉን ፣ ለስደት ሲዳርጉን ፣ ሲከፋፍሉንና ሲለያዩን ብሎም አንዱን የደገፉ መስለው ካንዱ ጎን ቆመው ሌላኛውን ወገናችንን ሲያስጨርሱት / ሲያጫርሱት ዝም .... መጨረሻ የሌለው ትዕግስት፣ ለጽድቅ ቢሆን መልካም ባልን ። ግን በታሪካችን ያልሰማነው ግፍና በደል እየደረሰብን ዝም ፥ ማብቂያውን ማየት ይናፍቃል ። ማብቂያው እራሱ ሥልጣን ላይ ያለውን ፤ ይህን ሁሉ የሚያደርሱብንን ከሥልጣን ስናወርዳቸው ብቻ መሆኑን ደግሞ ስናይ ጥፋቱ ከኛው ሆኖ እናገኘዋለን ። ይኽ ድርጊታችን ካለማወቅ እንጂ ከፍርሃት አልነበረም። እኛም ተመቻቸንላቸው እነርሱም ተዝናኑብን ።

እኛም እምነታችንን በእግዚአብሕሔር ላይ ሣይሆን በድርጅት በቡድን ወይ በግሰብ ላይ (በተለይ ዶክተር ሲባል የምንም ዶክተር ይኹን ልክ መድሃኒት መፈወሻ ያለው ይመስል ያለን እምነት የብቻው ነው ። እስከ ዛሬም የአስተሳሰባችን አካል ሆኖ አብሮን አለ) ሌላ ጊዜ እያፈራገጡ ለዚህ ያደረሱንን ባዕዳን ላይ ተስፋችንን ስንጥል ። በራሳችን ሁኔታውን መቀየር የሚያስችለን ኃይል ፈጣሪ የሰጠን እያለን ግን በራሳችን እምነት ስናጣ ፥ ማዘናጊያ ሚርታቸውን በመንገዳችን አኍረው ዓቅጣጫ ሲያስቱን ። ለጆሮ የሚከብድና ለኅሊና የሚሰቀጥጥ ነገርን በአንዳችን ፈጽመውብን ይኽ ተደረገ ስንባል፤ ያዙን ልቀቁን ስንል ። ምድረ አሜሪካንና አውሮፓን ሰልፍ በሰልፍ ስናደርገው ፣ ሻማ ስናበራ .... እኒህ ሰዎች ተበድለው ከፍቷቸዋል ያለን አንድስ እንኳ አላገኘንም ። እነሱም እንደ ውዳሴ እንደ ምስጋና ወሰደውብን ። እኛም ይኽን ስናደርግ ይኸው 27 ዓመት ደፈን ። ትግል ብለን መታገል ከጀመርንም ወደ 50 አመት ገደማ እያስቆጠርን ነው ። አንዳንዴ የሌለብን እርግማን ያለብን ይመስለኛል ። እናም ያልተበደርነውን እየከፈልን እንገኛለን ። በአእምሮ ደረጃ አስተሳሰባችንን ለመለወጥ ፣ በርዘውና አደንዝዘው እንድንመቻቸው የሚያደረጉት ፤ የእርስ በርስ የመጠላላትና የመጠፋፋት የትግል አይነት እንድናደርግ በወኪሎቻቸው የሚያደርጉት ... ስትራቴጂ መረን የለቀቀና ምን ታደርጉናላችሁ ዓይነት በዕብሪት የተሞላ ነው ። ያልነኩትና ያልዳሰሱት ነገር የለም ፣ ህዝብን ከህዝብ የሚያቃርንና የሚያጋጭ መለያ የሆኑ የቀሩ የሉም ። ሁሉም በኛ ላይ ተፈትሸዋል ወይ ተሞክረዋል ።

በእምነታችን ሲመጡብን ፣ አብያተ ክርስቲያናት ሲያቃጥሉ፣ በስልምና አማኞች የሚደርሰውን ግፍ ሲያዩት ፣ እምነት ፣ ወግ ፣ ባህል ፣ ልማዳችንን ሙሉ በሙሉ ሊቀይሩት ሲሞክሩ .... ዝም ብሎ ማየትን የመረጥን ስንሆንስ ። ሁሉ ነገር በተገላበጠ ዘመን ላይ ተገኝተንስ ነገራችንን እንደ ማቃናት እኛው ስንገለባብጠውስ ምን ይባላል።

የሚገርመው የዘመኑ አላዋቂዎች አዋቂ ሆነውብን ፣ ምንም ለህዝብ ለአገር ደንታ የሌላቸው ፖለቲከኞች የፖለቲካውን መሪ ጨብጠው ሲዘውሩት ፣ ለራሳቸው ነገረ ዓለሙ ጠፍቶባቸው ውሉን ሲያጠፉብንና እንደ ወራጅ ተጋፊ ወንዝ ውሃ እንደወሰደው ሰው እየሳቅን ስንወሰድ ስንጠፋ ዝምን የያዝን ስንሆንስ ። ይኽ የላጭን ልጅ ብቻ ሳይሆን እራሱን ላጪውን ቅማል በላው አያሰኝም ብላችሁ ነው ። ሁላችንም በአዙሪት ተይዘን ፣ እንክርቱን ገና አልጨረስ ብሎን ጊዜው እንደ ጎማ እየተለጠጠ አላልቅ ሲለንስ ምን ይሉታል ። እሱ እግዚአብሔር ይብቃችሁ ይበለን እንጂ እንክርታችን እንደ እስራኤላያውያን የ40 ቀን ወይ የወሩ መንገድ 40 ዓመት ሆነብን ። ዘመነ እንክርቱም እረዘመብን ፤ እንሆ የእግዚኦታና የምህላ ጊዜ ፤ አባት ካገኘን ። የኛ ወላጆች የአባቶቻችን ዝናብ ሲቀር ወይ የሆነ ችግር ሲገጥማቸው ተሰባስበው ፈጣሪ ከመአቱ እንዲሰውራቸው ምህላ እግዚኦታ በማድረግ ከጥፋት ይድኑ ነበር ። እኛም ከአባቶቻችን ወይ ከባዕዳኑ ያልሆን ትውልዶች ። እውነት የርግማን ልጆች ፤ የካም ልጆች ብቻ ነን .... ነው ወይስ የያፈትም የሴምም ደም በውስጣችን አለ ። እንዴት የፈጣሪ በረከቱ ቸርነቱና ጥበቃው ራቀን ።

እንዴት ነው ፤ ይኽ ሁሉ የፖለቲካ ድርጀት በየዓይነቱ ቀለም ያሸበረቁ ባለ ባንዲራ ያዥ እያሉን ፣ አዋቂ ምሁራኑ ከምን ጊዜውም በላይ በበዙባት አገር ፣ መፍትሄ ብልሃቱ ሲጠፋን መጠርጠር ነው ። የፈረንጂ ዕውቀት ብቻውን ዕውቀት ቢሆነን ኖሮ ከችግራችን ወጥተን በአሁኑ ዘመን እንደነሱ እፎይ ባልን ነበር ። ነገር ግን ከሁለት ያጣን ሆነን የኛ አባቶች ያስቀመጡልን፤ ዕውቀት የተትረፈረፈባቸው እያሉን ናቅነው ። አውቀውት መናቅ ተገቢ ነው ቢባል እንኳ ምኑንም ሳናውቅ ናቅነው ። ብልጦቹ በዘረፋም በግዥም ... በተገኘው መንገድ ዕውቀት የታጨቀባቸውን ፤ ዕድሜ የጠገቡና

ያስቆጠሩትን መጽሐፍት ወሰደው ዕውቀታቸውን ሲያሳድጉ ፤ የኛን ወስደው የነሱን ሰጡን ። የጥፋታችን መጀመሪያ ከዚህ ይጀምራል ። እኛም የነሱን ዕውቀት ትምህርታቸውን መጽሐፍ ቅዱስ አደረግነው ። የሰው ሥራ መሆኑን ሁሉ ዘነጋን ። ለእኛም ለእርስ በእርሳችን ለንቀት ሆነብን ። የችግራችን መፍቴሄ ግን ሁሉም ያለው በእጃችን ነበረ ። ነውም ። በእጅ ይዞ ፍለጋ የጤና ነው ብላችሁ ነው ። ከእኛ መከባበር ፣ መተማመን ፣ ፍቅር ፣ አንድነትና መተጋገዝ ከመሃላችን አጥፈተን ሌላው ይቅር በመንገድ ስንተላለፍ የእግዚአብሔርን ሰላምታ ለመለዋዎጥ እንኳ  የተጠየፍን ሰዎች እስከ መሆን ደረስን ። የዘመኑ የዘረኝነት በሽታ ። ክትባቱ የጠፋለት በሽታ ። መዓቱን ያርቅልን ፣ እንደ ክፋታችንም አይክፈለን ። አይበቀለን ። በቃችሁ ይበለን ።

ምን ብለን እንተንትነው የተማሩ አዋቂዎቻችን እንደ  ዲዳና እጁ እንደተቆረጠ ሰው ሆኑብን ፣ እጅ እየአላቸው አይጽፉልን ፤ አፍ እያላቸው ዲዳ ከሆኑስ የሚያዩ የሚሰሙ ቢሆኑስ ዕውቀታችው ለኛ ከሞኝነት ይቆጠር እንደሁ እንጂ ምን ሊረባ ምን ሊጠቅመን ። የሁለት አለም ኗሪዎች ሆነናል ማለት ያስችላል ምክያቱም ....... እስከ ዛሬ የተሰጡት ትንታኔዎች ከትምህርትም በላይ ትምህርት በሆኑ ነበር ግን ሰሚ / ተቀባይ የሌለበት አገር ስንሆንስ ፤ ቀድመው የነቁቱ ምጣድ ላይ እንደ የሚቆላ ተልባ ተንጣጥተው ተንጣጥተው ተበትነው ተበትነው አረው አለቁ እንጂ ሰሚ ተገኝቶ አልተጠቀምንበትም ። እንዲያውም ባለፉ ሰማዕታት ምጸትና ንቀት የቀደመን ትውልድ ሆን እንጂ ። የምንኮራባቸው አልሆንም ።  ይኽን ዓይነት የተለየ ሁኔታስ የታየባት ብቸኛዋ አገር ሳንሆንስ ቀረን ብላችሁ ነው ። በጊነስ መጽሃፍ የሚያስገባን ከተገኘ ።

ዘመኑ እምቦጭ ፣ አመተ ምህረቱ እምቦጭ፣ዕለቱ እምቦጭ .... ሥር የሌለው የውሃ ተክል ፣ አጥፊ አውዳሚ አረም ። ምሳሌነቱ ህብረሰባዊ መሰረት ለሌላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና ለመንግሥት ..... ሰጥቻለሁ ። እናም ሁሉም እምቦጭ ያሉበት ጊዜ ። ይኽ የዘመን ስላቅ ሁሉንም ቁልጭ አድርጎ እያሳየ ነው ። ምንነትን በኮስሞቲክ ሊደብቁት የማይቻልበት ጊዜ ። በጉራ ፣ በማስፈራራት፣በጉልበት፣በፕሮፓጋንዳ፣በሽወዳ ፤ በመምሰልና ትግል የቆዩበትን ዘመን እየቆጠሩ በፉገራ .... ህይወታቸውን የመሠረቱ እምቦጭ ድርጅቶች ፣ የፖለቲካ አድማሱን ሸፍነውብን የኖሩበት ዘመን የተፈጸመበት ፣ የፍጻሜው ወቅት መድረሱን እምቢልታ የሚነፋበት ፤ ደወሉ የሚሰማበት ዘመን ።
ድመቶች ከገዢ አይጦች  ጋር ጉባኤ ለዘመናት ያደረጉባት አገር ። አገረ ኢትዮጵያ ። የልመና የልምምጡ ጊዜ ያለፈበት ፣ የመሸማገል ጉባዔዎች ተጨርሰው የተዘጉበት ፣  የፍርድ ጊዜው ደርሶ የፍርድ ዙፋኑ የተዘረጋበት ቀን ፥ ባላንጣዎች ለፍርድ በቀኝ በግራ የሚቆሙበት ዘመን ። የመጨረሻው መጀመሪያ ዕለት፣ ዕለተ ዓርብ ፣ የትንሣኤውን እሁድ አብሣሪ ዕለት ፤ ዕለተ አርብ ። በእምቦጮች ላይ ፍርድ የሚፈረድበት፣ ህዝብ የሚያቸንፍበት የነፃናትና የአርነት ጊዜ ፣ ዕለተ ሰንበትን በተስፋ የምናይበት ቀን ። ፍጻሜ እምቦጭ።

ያለፉቱ 27 ዓመት የፖለቲካ ድርጅቶች የመምራት ሚና የጠፋበት ። እንደ ቀደምቱ የመሪነት ሚና ለራሳቸው ሰጥተው እንደሚጎማለሉት የዚያን ጊዜ የሚጎማለሉበት ዘምን አስተሳሰብን ኮርጀው / ቀድተው የመሪነት ሚናን ደፍሮ ነኝ የሚል ባይኖርም ፤ ትንሽ ዘወር አድርገው በውስጠ ታዋቂነት ያደረጉ ወሬኛ ታጋዮች የሞሉበት ። ይኽ ግልጽነት የጎደለው አካሄድ ከፍራቻቸው የመነጨ ነውና በሽወዳ ደበቅ አድርጎ በመያዝ በጋራ ለሚደረገው ትግል በጋራ የሚጫዋቱበት ሜዳ ገና እየፈለጉ ያሉ ። እንዲያውም ደግሰው የያዙልን ፤ ..... ጊዜ በግርግር ገዝቶ በማዘናጋት ፤ ለሚደረገው ህዝባዊ ትግል እንቅፋት ለመሆን ፤ እራሳቸውን ለሥልጣን ለማብቃት ዓላማቸው አድርገው ያስቀመጡ መሆናቸውን ድርጊታቸው እያሳበቀባቸው ፤ ምንተ አፍረታቸውን ዋጥ አድርገው ፤ በፈገግታቸው ሸፍነው አያልፉት ሆኖባቸው ግን እንደ ንጉሱ እራቁታቸውን ቆመው የሚታዩበት ፤ ለዚህ ግልጽ ለሆነ ድርጊታቸው ምሲጥር አድርገውብን በድርቅና ሊደብቋቸው እየከጀሉ ያሉ አደናጋሪ ኃይላት በየዓይነቱ አሏቸው ።  ይኽን ሥራቸውን እንጀራ ያደረጉት / የያዙ አዳናጋሪዎቻቸው ሌት ከቀን ይታኩኑላቸዋል ። ግን ንጉሱ እራቁታቸውን ናቸው ... እንደ ህፃኑ ልጅ ንጉሱ እራቁታቸውን ናቸው የሚል ስለሌለ ሁሉ አዋቂ የሆነበት የመከባበር ዘምን ። እንዴትስ ይታረሙ .. አራሚ የጠፋባት ሳይሆን የፈራበት ዘመን ።

የእነዚህ  ድርጅቶች አካሄድ ካለው መንግስት ህልፈትም በኋላም የሚኖረው የአላማቸው ልዩነት ቅራኔው የማይታረቅ ሆኖ አገራችንን ወደ ትርምስ ፣ እመሳና አለመረጋጋት  እንደሚከታት  ግልጽ  ነው  ።  ለዚህም  ነው  አንዳንዶች ለህዝባችን  ባርነትን  የሚመርጡት  ።  የጠላቶቻችን የሻቢያን የወያኔን ብልጠጥ አይነት በመከተል ፣ በትግሉ ወቅት ሌሎችን አጥፍቶ ራስን ማንገሥ ከእንጊዲህ እንደማይችል ማወቅ ይኖርባቸዋል ። ይኽ አካሄድ  ለጊዜው የጠቀመ ለእነርሱ ለሻቢያንና ለወያኔ ብቻ ነው ። ነበርም ። ለአረጀ ውሻ አዲስ ትሪክ  አያስተምሩት  እንደሚባለው.......  እንደማይሠራ ለተተኪዎቻቸው ማን በነገራቸው ። ለክፉ ክፋቱ በራሱ ይበቃዋል የራሱ ክፋት ያጠፋዋልና ። በጊዜ ካልገባቸው

ይጠፉበታል ። እናም ቤት ይቃጠላል እንዳለው ሰው ማስጠንቀቃችንን እንደጅል አትቁጠሩብን ። አትጠየፉብን ። የአገር ነገር ከ"ሆድ ይቆርጥ" በላይ ነውና እንዴት ዝም ልንልስ ይጠበቅብናል።

በተለይ የህዝቡን መነሳሳት ምን ዓይነት መልክ ይዞ እንደሚነሳ አናውቅም ። የሚያውቅም የለም ። በጦርነት ተጀምሮ በሰላም ይጠናቀቅ ወይ በሰላም ተጀምሮ በጦርነት ይፈጸም ወይ በጦርነት ተጀምሮ በጠርነት ይፈጸም የሚያውቅ የለም ። ነገር አለሙ ከግምት ውጭ ነው ። ሻዕብያም ወያኔን ለማዳን በወንድምነት ተነሳስቶ ወይ ገፉፊ ኃይላት ገፍተውት ወይ ወያኔን የሚተኩትን በዙሪያው ኮልኩሎ የያዛቸውን ልጆቹን አስተባብሮ በመግባት እነሱን ረድቶ ስልጣን አውጥቶ ለወያኔ እንዳደረገው ሥልጣኑን ለማስጠበቅ ልሞክር ብሎ ሊገባ ይችላል ወይ ጣልቃ እንደገባ ፣ እሱም በሚጠላት ምድር ዘመኑ ይፈጠም ይሆናል ። የሚታወቅ ነገር የለም ። በዚህ ጊዜ ነብይ በመሃላችን የለምና የሚፈጸመውን ማወቅ አንችልም ። እነሆ ያለንበት ወቅት አስቸጋሪ ወቅት ብቻ ሳይሆን አስፈሪና አስጨናቂም ጊዜ ነው ። ፍጡር ነንና በእንጠፉ ወይ በእንድን መሃል ፤ በሃሳብ ተወጥራ የምትሰቃይ ሥጋና ነፍስ ለብሰን የተሸከምን ሰዎች ። ስለሆነም ለማንም ኢትዮጵያዊ ይኸን ሁኔታ ተቀምጦ ማየት ኀጢያት ይመስለኛል ። በግሌ ብናደርግ የሚለውን እነሆ ። መልካም ንባብ ይሁንላችሁ አስተያየት ተለዋወጡበት መፍቴሄው ከኛው ነውና እንጨነቅበት እንጠበብበት ። ከሌሎች መጠበቅ ግን ስንፍና ነውና እስከ ዛሬ የተኛነው ይበቃል፤ እንንቃ ተነስተንም ሥራችንን እናቀላጥፍ ። በትግሉ ወይ በሰዎች / በግለሰቦች ተስፋ ቆርጣችሁ በሌላ ዓለም በማይታየው የምትኖሩም ወደ ተዋችሁት ምድር አገር ተመለሱ ። የጀመሩትን ሲጨርሱት ደስ ይላልና ደስታችሁን ያዟት ።

 ዓላማው ርዕዮቱ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት (ህዝባዊነት)ነው ። ማንም ግለሰብ ይሁን ቡድን ወይ ድርጅት ይምጣ ይኸን አስተሳሰብ የበላይ ሊሆን የሚችል ወይ ሊበልጥና ሊተካ የሚችል የለም ። ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን እንጂ የሌላ የማንም አይደለችም ። ሰዎቿም ባንዳ ከሃዲ አይደሉም ። አሁንም ለወደፊቱም ባንዳዎች ይኸችን አገር አይመሯትም ። እንደ ህዝብ እራሱን ለመምራትና ለማስተዳደር በዘመኑ በቂ ትምህርትን የገበየ ህዝብ ነውና። ሲኖርም የኖረው እራሱን በራሱ እያስተዳደረ የኖረ ሕዝብ ነው ። ይኸንም በተደጋጋሚ በታሪኩ መንግስት በሌለበት ፣ ወይ የመንግሥት ሽግግር በሚደረግበት ጊዜ ወይ ሥልጣን ባዶ ሆኖ ክፍት በሆነበት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በወደቀባቸው ጊዚያት ምን ዓይነት ሕዝብ እንደሆነ አስመስክሯል ። አሁንም በዚህ መንግሥት ሥር እያለ እንኳ በአንድነት እየኖረ ነው ። አገሪቷም አገረ እግዚአብሔር የተባለችው ለዘበት አልነበረም ስለሆነች እንጂ ።

አሁን ለመሰባሰብና ለመደራጀት አመቺ የሚሆነው በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ነው ። ብዙዋቹ እንደማይቻል ያለውን ሚና አሳንሰው ሲነግሩን ቆይተዋል ። ነጋሪዎቻችንም በውጭ የተደራጁ ኃይሎችም በውስጥም ያሉት ድርጅቶች ዋነኛዋቹ ናቸው ። የወያኔ የሻቢያም እጅ የለበትም አልልም ። ለምሳሌ ከሚባለን እንነሳ .. በኬንያ መግባት አይቻልም ፣ በሶማሌ አይቻልም በጁቡቲም አይቻልም የሚቻለው በኤርትራ ብቻ ነው ይሉናል ።ትግል እነሱ ብቻ በሚያውቁት ስልት ብቻ ይሄድ ይመስላቸዋል። ትግል የትጥቅ ትግል ብቻ እንደሆነና ያውም እነሱ ባለፉበት መንገድ እንደሆነ ይነግሩናል ። ዙርያውን ገደል በማድረግ የሚጠቀሙበት ፕሮፓጋንዳ መሆኑ ነው ። ምርጫ በማይሰጥ ሁኔታ ውስጥ በፕሮፓጋንዳቸው ተቦትልከን ተዘናግተን እጃችንን አጣጥፈን እንድንቀመጥ ይፈልጋሉ ። ሞኝ ከተገኘ ብለው ነው መሰል በፕሮፓጋንዳቸው ድርቅ ብለውበታል ። ተከታይም አላገኙም ማለት አይቻልም ። ግን እነዚህ የተቀበሏቸው ውርደታችን ናቸው ። አምባገነኖች ሁሌም ሕዝብን ይፈሩታል፤ ስለሆነም ታሪክ ሠሪ የሆነውን ኃይል፤ ኃይል እንደሌለው ለማሳየት በተለያዩ መንገዶች ይጥራሉ ። ..ወዘተ ... ። የነሱን ለነሱ ትተን እኛ በምንፈልገውና በሚያዋጣ የትግል ሥልት ተደራጅተን ልንታገል ይገባናል የማንንም ዕራዳታ አንፈልግም ።

እንደ ህዝብ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አቅም ፤ ጉልበቱና ኀይሉ አለው ፣ ታሪክም እራሷ ኃላፊነትን ጥላበታልች ፤ ከዚህ ሃቅ መሸሽ አይቻለንምና ደፍረን ልንቀበል ይገባል ። ጊዜውም ያለንበት ቦታ / ሥፍራ ይፈቅዳልና ። ይኸን አደራ ተቀብለን ለመውሰደም ደፋሮች ልንሆን ይገባል ። ሌላ ምርጫም ያለን አይመስለኝም ። ዕድላችንም የተቆራኘው ከዚሁ ጋር ነውና ባለው መንገድ ተደራጅትን ከመታገል ውጭ ሌላ የነጻነት ጎዳና የለንም ። ሁሉንም ነገሮች ሞክረናቸው አልሠሩም ። ምክንያቶቹ ብዙ ናቸውና መዘርዘር የሚያስፈልግ አይመስለኝም ።

ስለሆነም ሠፊ በሆነ ማሕበር በአንድ ተሰባስቦና ተደራጅቶ ከመነሳት ውጪ ሌላ መንገድ / አማራጭ የለንም ። ለምስረታው መነሻ የሚመስሉኝ በየቦታው ያሉ የኢትዮጵያኑ ማኅበራት (Ethiopian community associations)፣ የተለያዩ ቀድሞ አገር ቤት በሙያቸው የተደራጁ ማኅበራት፣ በውጭም በሙያቸው ተደራጅተው ያሉ ማኅበራት ፣ አሁን

ብቅ ብቅ እያሉ ህዝብን እያስደመሙ ያሉት ማህበራት ... እንደ ጎንደር ጎጃም ወሎ ሸዋ ... ያሉት ማህበራት ፤ የተለያዩ ስም ይዘው እየተንቀሳቀሱ ያሉ የሰባዊ መብት ይኹን ሌሎች በተለያዩ የመሰባሰቢያ ማዕከላት ተሰባስበው ያሉ፣ የሃይማኖት ስብስቦች በዋናነት ሁለቱ ኢትዮጵያዊ እምነቶችን የሚወክሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት (የተዋህዶ ኦርቶዶክስና የእስልምና እምነት ተካተዮችን ያቀፉ ማኅበራት..... ወዘተ )፣በየቦታው ያሉ ሬድዮ ጣቢያዎች ፣ ነጋዴዎች በተለያዩ ሥራ ያሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ወዘተ .... ሁሉንም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የማኅበሩ ዓባል ሊሆኑ የሚችሉበትና እንደየችሎታቸው እያንዳንዱ ግለሰብም ለአገሩ ለህዝቡ አስተዋጽዎ የሚያበረክትበት ዕድል የሚሰጥ **<u>ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያኑ ማኅበር የፖለቲካ ይዘት ያለው ያስፈልገናል</u>** ። በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊውን አሰባሳቢና መሥራች አካል/ አካላት በየቦታው ተመሥርተው እየተገናኙ ሥራቸውን / የማሰባሰብንና የምስረታ ሥራ ማድረግ ይችላሉ .....ወዘተ... ። አገር ከጠፋች ወይ ከተበተነች ወይ በማያበራ ትርምስ ውስጥ ከገባች በኋላ መመለስ ከባድ ነውና ከወዲሁ ከመታገል ውጭ ሌላ መፍትሄ ያለን አይመስለኛም ። በጅቡቲ ፣ በሶማሌ ..... ሰፍረው ያሉ የባእድ ጦሮች ለምን የተዘጋጁ መሆናቸውን ባናውቅም ። በማረጋጋት ሥም ...ወዘተ ሊገቡና ለሌላ ላልታሰበ ችግር ሊዳረጉን ይችላሉ ። ስለሆነም ለእኛም ላገርም ስንል ጊዜው አላለፈብንምና እንሰባሰብ እንደራጅ ። ገፋፊ ኃይልንም አንጠብቅ ። ለሚንቁንም እናሳፍራቸው ፣ ማሳፈርም እንችላለንና ። አሁን ወያኔ የሚያደርገውን ሲያዩት ለዚህ ነው የሚፈፀመው/የፈፀመው ለማለት ምክንያት ብንፈልግ ቀጥተኛ የሆነ መልስ አናገኝም ። ሁሉን ሸፍነው ነው የሚያስኬዱት ። ምክንያቱ እሩቅ አይደለም እኛም እየለፋን ያገኘነው ዋናው መፍቴ አድርገን የወሰድነው እነሱ (ወያኔዎቹ) የሄደበት የመፍትሄ መንገድ ይዞ መንጎድን ነው በአብዛኛው የመረጥነው ። እራስን በራስ መበተን ፣ ኢትዮጵያን የማጥፋት የትግል ስትራቴጂ ይላችኋል ይኸ ነው ።

የፖለቲካ ድርጅቶች ሊመሩን የሚችሉ፣ ከፊት ሆነው እየመሩ፣ ከህዝብ ጋር ቆመው እየሞቱ የሚያሳዩ ፣ እየወደቁ የሚነሱ ለህዝብ የጀግንነት ምሳሌ አርአያ የሚሆኑ በዚህ ዘመን የሉንም ። አላገኘንም ። ያሉን ከኋላ የህዝቡን ትግል የሚከተሉ አድፍጠው ከኋላ ተከታዮች ናቸው ። ስለሆነም ዝም ብለን የምናይ መሆን የለብንም ። ለዚህ ካልታደልን እራሳችን ለራሳችን ተነሳስተን ልንሰባሰብ ፣ ልንደራጅና ትግሉን የተለየ መልክ እንዲይዝ ማድረግ እንችላለን ። በየምንገኝበት አገርም ፤ በአንድ ሆነን ፤ ከማኅበራችን ከፊት ከኋላው ቆመን በየአለንበት በሚካሄዱ ምርጫዎች በመሳተፍ ሆነ ፣ ሎቢ በማድረግ ፣ የዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን በመሥራት ፤ ለራሳችንም በትምርት ይሁን በኑሯችን ደረጃ ሳይቀር ለበጎ ነገር ልንጠቀምበት እንችላለን ። ወዘተ....ወዘተ...... ። ስለሆነም ፖለቲካዊ ይዘት ያለው የብዙኀን ማህበር ያስፈልገናል ። አጠቃላይ በውጭም ይሁን በውስጥ የምናካሂደውን ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ትግል ፤ በፖለቲካው ይሁን በኤኮኖሚያዊው ወይ በማኀበራዊ ደረጃ በብዙ መልኩ ልንታገልና ለአገራችንም ልንጠቀም እንችላለን ። በአንድ አስተባብሮ ያለውን የአርበኝነት ትግል መልክ ባለውና በተቀናጀ ደረጃ የሚያሰተባብር ፣ የተቃውሞው ትግል በአገር ደረጃ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖረው ለማድረግ ፣ ነፃ በወጡባቸው አካባቢዎች ህዝባዊ አስተዳደሩ መልክ እንዲይዝ ለማድረግ ፣ ታጋይ አርበኞችን የሚረዳና በየቦታው እንዲመሠረቱ የሚደግፍ ፤ አጠቃላይ ትግሉን ማስተባበር የሚችል ማኅበር ፣ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያኑ ማኅበር ..... መደብ ፣ ጎሳ ፣ ቋንቋንና ክልልን ...... መሠረተ ዓላማው ያላደረገ **<u>በዕውቀት ፤ በትምህርት ፤ በምርምርና በጥናት</u>** የሚመራ ድርጅት ያስፈልገናል ። ለዚህ ሙሉ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሕዝባዊ ድርጅት ፤ ለትግሉ የሚረዳ ብቻ ሳይሆን ሕዝብን ለድል የሚያበቃ ፤ ከድሉም በኋላ አገሪቱ በዕድገቷ የተረጋጋ ጉዞ እንድታደርግ ፤ በፖለቲካው በኤኮኖሚው ሆነ በማኅረሰባዊ ጉዳዮች ዕድገት ላይ አስተዋጾ ያለው አርበኛ ድርጅትን / ማኅበርን መመሥረት ይገባናል ። ያለንን የሰው ኃይል በአግባቡ ተመድበው ለትግሉም ለአገርም የሚጠቅሙ ማህበራትን በሥሩ ሊቋቋሙና ለብዙ ሥራዎች ልንጠቀምባቸው እንችላለን ..... ። ከላይ እስከታች ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ፣ በስፋት አገሪቷንና ህዝቡን የያዘና ያደረሰ ፤ ለሕዝብ የቆመ ተቋም መመሥረት መቻል አለብን ። ግድም ይመስለኛል ፣ የሞኝነቱን ዘመን አልፎን እንዲጠፋ ማድረግ አለብን ።

እዚህ ላይ የውክልና ዴሞክራሲን መነካካት አልፈልግም ። ነገር ግን የተደራጁቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ግን ከእንግዲህ በህዝብ ላይ ሊመጻደቁበት አያስፈልግም ። ከኑግ ... ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ነውና ካለ ኅጢያታቸው ለተወቀጡት ባዝንም ምርጫ ግን ያለን አይመስለኝም ። በዚህ ጽሑፍ ከስብስቡ የፖለቲካ ድርጅቶችን ለማስገባት አልፈለግኩም ለዚህ ምክንያቶች አሉኝ ። አንዱ ያለመታደል ሆኖ የያዙት የፖለቲካ አላማቸው እርስ በራስ የሚያጠፋፉና የቅራኔና የችግር አፈታታቸው ዘዴ ብልሃቱ እርቅንና መስማማት መሠረት ያደረገ አይደለም ። በትግላችንም አብዛኛው መድረኩን የያዙት እንዚሁ ኃይላት ናቸው ። ስለሆነም እነሆን ገና አመለካከት አስተሳሰባቸውን ሳይያርሙ መጨመሩ ለእንቅፋት ስለሚሆኑብን መጨመሩ አልታዩኝም ።

ይህ ድርጊታችን ለሌሎች ወንድም አፍሪካውያን አገሮችም ምሳሌ የሚሆንም ይመስለኛል ። አፍሪካ ከ1250 – 3000 ቋንቋ የሚነገሩባ ት ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር የሚታይባት በዚኽ ምዕተ ዓመት መጨረሻ የህዝቧ ቁጥር 4 . 4

ቢሊየን ያልፋል እየተባለ የሚነገርላት ከዓለም የሕዝብ ብዛትም ወደ 40 % ገደማ ትሸፍናለች የምትባል አሃጉራችን አፍሪካ ፤ ከኛ ከልጆቿ ብዙ ትጠብቃለች ። አሁንም ፤ በድጋሚ የነፃነት ምልክት የንጋት ኮከብ ልንሆን እንችላለን ።

__*ለየት ያለ አዲስ የፖለቲካ አካሄድ እንደ አገር ነፃ የሆነች ፤ ከማንኛውም አገር ቀጥተኛ ቁጥጥር በፖለቲካውም በኤኮኖሚውም መስክ ነፃ የወጣች እንድትሆን አገራችንን እንፈልጋለን*__ ። ይኽን ከፈለግንና ካልን ማድረግ እንችላለን ። በአሁኑገዜ ይኽን ለማድረግ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ እየተመቻቸልን ያለበት ነው ። ዓለም በለውጥና በኃይል ሽግሽግ ውስጥ እየታመሰች ያለችበት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለችው ። ይኽ የሽግሽግ ጊዜ ይርዘም ይጠር ሁኔታው የሚወስነው ቢሆንም ፣ ሽግግሩ ግን ሰላማዊ እንዲሆንና ለዓለም ሕዝቦችም ይኹን አገሮች የተመቸና የተሻለ ሁኔታን አምጪ እንዲሆን እመኛለሁ ። የአንደኛውና የሁለተኛው የአለም ጦርነት አይነት እልቂት የተሸፈነ ሦሥተኛ ታሪክ አንፈልግም ። ለእኛ ግን መሸሎኪያ መንገድ የምናገኝበት ወቅት ይመስለኛል ። ይኽን ጊዜ ለመጠቀምም ዕውቀቱን ትምህርቱን ብልሃት ስልቱን እግዚአብሔር ያድለን ።

የማኅበሩ አጭር ጊዜ ዓላማው በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን ህዝባዊ የአርበኝነት ትግል የተሳካ እንዲሆን ለማድረግና "ሕዝባዊ መንግሥት" በተግባር ሕዝባዊ መሠረቱን የያዘ እንዲመሠረት ለመርዳት ነው ። የረጅም ጊዜ ዓላማው የተረጋጋች ኢትዮጵያን የሚያልም ፤ ለዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች ከህዝብ በላይ የማይሆኑበትን የፖለቲካ ሥርዓት ወይም ህዝቡ በቀጥታ የመንግሥት ባለቤትነቱ የሚረጋገጥበት ፣ የዚኽም ዝርዝር ጉዳዮቹ በህገ መንግሥቱ ሕዝብ ተወያይቶበት በግብር የሚውሉበት፤ ከተራ አስተዳደራዊ መዋቅር ጀምሮ ሁሉም አካላት ሕዝባዊና ሙያተኛ በሆኑ ሙያተኞች ሥራዎች የሚከናወኑበት ፣ በማንኛውም በመንግሥታዊ አስተዳደር ሆነ አካል የሕዝባዊ መንግሥቱን / ሕዝብን አገልጋይ እንጂ ከሕዝባዊ አገልግሎት ውጭ ምንም ማድረግ እንደማይችል የሚያረጋግጥ .... ። ከዚህ አንጻርም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥራና ፣ኀላፊት ፣ ዓይነትና ብዛት የሚደነግግ ሕግ የሚኖርበት ። የመንግሥት የኃይል መዋቅር ለሕዝብም ለአገርም ጠቃሚ በሆነ ደረጃ የሚደራጁበት ፣ ሥራው ድንበር ያለው መሆኑና ይኽን የሚያሳይ ግልጽ መምሪያ ያለው መሆን አለበት ። ንቅዘት ሆነ አድልዎ በየትኛውም መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ የማይታይባቸው ማድረግ ። ጤና ትምህርት በትክክል ለሕዝብ የሚዳረሱበት እንደ ትልቅ አገራዊ ተቋም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥበት ፤ በዚህ ሙያ የሚሠማሩት ምርጥ የአገሪቷ ልጆች ተመድበው የሚሰለፉበት ማድረግ ። ከሙያተኛም ከሕዝቡም በወጡ ልጆቹ የተደራጀ ሕዝባዊ መከላካያ ኃይል ከዘመኑ ሥልጣኔ ጋር የሚጣጣም መምሥረት ወ.ዘ.ተ... የሚሆንበትና የምናይባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚረዳ ማኅበር ያስፈልገናል ።

ምኞት አይከለከልምና አሁን ካለንበት ችግር ተወጠን እራሳችንንም አደላድለን ለመጪው ተተኪ ትውልዶች አገሪቷን እንደቀድሞ አባቶቻችን የዓለም ቁንጮ እንዲያደርጓት መሠረቱን ለመጣልም የሚያስችል ራይን ይዘን ልንነሳ ያስፈልጋል ። ይኽ ጉዳይ አሁን ላለው ትውልድ ታሪክ አደራ የጣለችበት የማያልፈው ጉዳይ / ነገር ሊሆን ይገባል ። ካላማረብን ታሪካዊ ኀላፊነቱን አልቀበልም ካለን ቀጣዩ ትውልድ ተረክቦ ይወስደዋል ። ኢትዮጵያ አገራችን ብዙ እንግልት ደም መፋሰስን ታይ እንደሁ እንጂ የምትጠፋ አገር አይደለችም ። የሚያስፈራውን እሱ ፈጣሪ ሸፍኖ ሳናየው ያሳልፍልን እያልኩ ጽሁፌን እጨርሳለሁ ። እናንተም ተወያዩበት ፣ የሚታረመውን አርማችሁ ወደ አደገ አስተሳሰብ ከፍ እናድርገው ። የደፈረ መውጫ አያጣምና ወደ መፍቴሄው መድረስ እንችላለን ። ለዚህም ሕዝባዊ ሆነን እንነሳ የሚያስፈልገው ይኽ ነውና ።

ለመሰባሰብም እርስ በርሳችን ተከባብረን ልንተገብረው ይገባል ። አገራችን ትልቅ አገር ናትና እናከብራት ፤ ብዙ ፀጋዎች ያሏት አገር ናትና እኛም ለተወለድንባት አገራችን ተባብረን ከዚህ የላቀ ትልቅ ልናደርግ እንችላለን ። እራሳችንን ችለን እንዳንቆም ለሚፈልጉ እግዚአብሔር አሳባቸውን ከልቦናቸው ያጥፋው ፣ አባታችን ተክለ ኀይማኖት በጉራጌ የጠንቋች አለቃ (በቢለት ተራራ ኗሪ የነበረውን) ከነተከታዮቹ ምድር ተከፍታ እንድትውጠው እንዳደረጉት ፤ ለአገራችን ለኢትዮጵያ አርነት ብለን የምናደርገውን ይኽን መሰባሰባችንን ጠልተውብን.... እንዳንሰባሰብ የሚነሳሱብን ጠላቶቻችንን እነሱንም ምድር ተከፍታ ትዋጣቸው ። አሜን ።
ለኛም ልቦናውንና ማስተዋሉን ከልቦናችን ይጨምርልን
። አሜን ።